በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ጸሎትና ሥርዓቱ

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከ12፡30 – 1፡30 ምሽት

**ኅዳር ፲፮ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.**

# ጸሎት

- ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ሁሉ የሚፈጸመው በጸሎት ነው።
- ጸሎት፡-
    - ልመና፡ ስዕለት፡ ምስጋና ነው።
    - ተናግሮተ ሰብእ ኀበ እግዚአብሔር ልዑል፡- ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገረው ምስጢር ነው።
    - ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ የሚያገናኝ በሃይማኖት ላይ የተመሠረተ ልባዊ ጥያቄ ነው።
- ጸለየ ለመነ ከሚለው የግእዝ ቃል የተገኘ ነው። ቀጥተኛ ትርጉሙም መለመን፣ መሳል፣ መማለድ፣ መማፀን፣ የሙጥኝ ማለት ማመስገን ነው።

*<u>የጸሎት ዋና ዓላማው ምንድር ነው?</u>*

- ባለፈው እግዚአብሔርን ለማመስገን። "እግዚአብሔር ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ ለስሙ ዘምሩ" *<u>መዝ 135፡1-ፍጻሜ</u>*።
- ለሚመጣው እግዚአብሔርን ለመለመን። "እንደ ዓይን ብሌን ጠብቀኝ፥ በክንፎችህ ጥላ ሰውረኝ" *<u>መዝ 17፡8።</u>*
- ጌትነቱን ለማመን። "ሁሉን ቻይ አምላክ እኔ ነኝ" እንዳለ *<u>ዘፍጥ 35፡11።</u>*
- በደልን ለማመን። *<u>ማቴ 15፡21-28።</u>*
- እግዚአብሔርን ወይም ራስን ደስ የሚያሰኙበትን ነገር ሽቶ ተመኝቶ ፈልጎ ወይም ፈቅዶ ሁሉን ማድረግ ወደ ሚችል ወደ እግዚአብሔር ለማመልከት ወይም ለመጮህ ነው። *<u>1ኛ ሳሙ 1፡1-ፍጻሜ።</u>*

# ጸሎት የምንጸልየው እንዴት ነው?

1. በእግር ቀጥ ብሎ በመቆም፡፡ "ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ" እንዳለው ማር 11፡25፡፡ "በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር::" ሉቃ 1፡10፡፡ ቀዳ ነገ 8፡22፣ ካል ዜና 5፡14፣ኢዮ 30፡28፡፡
2. ወገብን በዝናር በመታጠቅ በማደግደግ ነው፡፡ "ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን" ሉቃ 12፡35፡፡
3. ፊትን ወደ ምስራቅ በመመለስ፣ ልቡናን ሳያባክኑ ነው፡፡ "በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣ ለእግዚአብሔር ዘምሩ " መዝ 68፡33፡፡ "ስለዚህ እግዚአብሔርን በምሥራቅ፥ የእስራኤልንም አምላክ የእግዚአብሔርንም ስም በባሕር ደሴቶች አክብሩ::" ኢሳ 24፡15፡፡
4. ፊትን በትእምርተ መስቀል ምልክት በጣት በማማተብ ነው፡፡ "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው:: እርሱንም በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታልና::" ቆላ 2፡14፡፡
የምናማትበው፡- ጸሎት ስንጀምርና መስቀልን የሚያነሳ ቃል ሲኖር ሆኖ ከላይ ወደታች ከግራ ወደ ቀኝ ጣቶቻችንን በመስቀል ምልክት በማድረግ ነው፡፡

- አለመጸለይ ኃጢአት ነነው፡፡ 1ኛ ሳሙ 12፡23፡፡

## ስንጸልይ የሰውነታችንና የድምጻችን ሁኔታ እንዴት ነው?

1. ድምጽ፡-
   - በጩኸት በማንበብ፡፡ ማር 10፡46-52፡፡
   - በለሆሳስ በመድገም፡፡ 1ኛ ሳሙ 1፡12-18፡፡
   - በኅሊና በማሰብ፡፡ ሉቃ 8፡42-48፣ ሉቃ 2፡43-48፡፡
   - በጣዕመ ዜማ፡፡ "በማኅበርም መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ::" ዕብ 2፡13
2. የአካል ሁኔታ፡-
   - እጅን አንስቶ በመዘርጋት፡፡ "ወደ መቅደስህ ማደሪያ እጄን ባነሣሁ ጊዜ፥ ወደ አንተ የጮኽሁትን የልመናዬን ቃል ስማ::" መዝ 28፡2፡፡
   - ዓይኖችን ወደ ሰማይ በማቅናት፡፡ "በሰማይ የምትኖር ሆይ፥ ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ::" መዝ 122፡1፡፡ "አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ" ማቴ 14፡19፡፡
   - ደረትን በመድቃት፡፡ ሉቃስ 18፡9-14፡፡
   - በመተከዝ ለሚቻለውም በለቅሶ፡፡ 2ኛ ነገ 20፡1-7፡፡

# ጸሎት…

## *የሚጸለየው ምንድር ነው?*

1. በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው አቡነ ዘበሰማያትና ጸሎተ ማርያም ነው፡፡ ማቴ 6፡9-14፣ ሉቃ 1፡26-55፡፡
2. በቀኖና በሊቃውንት መጽሐፍ እንደተጻፈው ጸሎተ ሃይማኖት፣አብዝቶ ለመጸለይ መዝሙረ ዳዊት ነው፡፡
3. ለካህናት ግን ከዚህ ሁሉ ጋር ከኦሪት ከነቢያት የተውጣጣ ሊጦን፣ መስተብቁዕ፣ ኪዳን፣ ውዳሴ ማርያም፣ ቅዳሴ ማርያም፣ አርጋኖን… እንዲጸልዩ ታዟል፡፡

## *በየቀኑ ጸሎት የሚጸለይባቸው ጊዜያት ስንት ናቸው? መቼና መቼ? ለምን?*

- "ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ፡፡" *መዝ 118፡164* እንዳለ በየቀኑ ጸሎት የሚጸለይባቸው ጊዜያት ሰባት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-
    1. *ነግህ (ማለዳ)*
        - ጽልመተ - ሌሊቱን አርቀህ ብርሃነ መዓልቱን ያመጣህልን በማለት፡፡ "ማልደው ተነሥተው በእግዚአብሔር ፊት ሰገዱ" እንዳለ *ቀዳ ሳሙ 1፡19፡፡*
        - የሁሉ አባት አዳም የተፈጠረበት ስለሆነ፡፡ *ዘፍጥ 1፡26፡፡*
        - ጌታችን በጲላጦስ አደባባይ ቆሞ የተመረመረበት ሰዓት ስለሆነ በነግህ እጅን ታጥቦ መጸለይ ይገባል፡፡
    2. *ሦስት ሰዓት*
        - የሁሉ እናት ሔዋን የተፈጠረችበት ሰዓት ስለሆነ
        - እመቤታችን ብሥራተ መልአክን ሰምታ ጌታን የፀነሰችበት ስለሆነ፡፡ *ሉቃ 1፡26-28፡፡*
        - ጌታችንነ በጲላለጦስ ፊት የተፈረደበት ስለሆነ፡፡ *ማቴ 27፡24-31፡፡*
        - በጽርሐ ጽዮን መንፈስቅዱስ ለሐዋርያት የወረደባት ስለሆነ፡፡ *የሐዋ. ሥራ 2፡1-47 (15)*
    3. *ስድስት ሰዓት*
        - አጋንንት የሚሰለጥኑበት ስለሆነ አድነን ለማለት፡፡
        - አዳም የካደባት ስለሆነ ከክህደት አድነን ለማለት፡፡
        - ጌታ የተሰቀለባት ስለሆነ ያየንን በማሰብበ በቀትር መጸለይ ይገባል፡፡ *ማቴ 27፡45፡፡*
    4. *ዘጠኝ ሰዓት*
        - መላዕክት የሰውን ምግባርና ጸሎት የሚያሳርጉበት ስለሆነ አሳርጉልን ለማለት፡፡
        - ጌታችን ቅድስት ነፍሱን ከሥጋው የለየባት ስለሆነች ሞቱን በማሰብ፡፡ "የዘጠኝ ሰዓት ጸሎት በቤቴ እጸልይ ነበር፡፡" *ሥራ 10፡30፣ 10፡3፣ 3፡1፣ ማቴ 27፡46፡፡*

# ጸሎት…

5. *ሠርክ (አሥራ አንድ ሰዓት)*
   - ሰው ሲሠራ ውሎ ዋጋውን የሚቀበልበት ስለሆነ በጎ ዋጋችንን ስጠን ለማለት፡፡ "በሠርክም መሥዋዕት ጊዜ ልብሴና መጐናጸፊያዬ እንደ ተቀደደ ሆኖ ከመዋረዴ ተነሣሁ በጕልበቴም ተንበርክኬ ወደ አምላኬ ወደ እግዚአብሔር እጄን ዘረጋሁ፡፡" እንዳለ *ዕዝራ 9፡5፡፡*
   - ጌታችን ወደ መቃብር የወረደበት ስለሆነ፡፡ *ማቴ 27፡56፡፡*
6. *ከመኝታ በፊት*
   - የሥራውንነ ጊዜ አሳልፈህ የዕረፍቱን ጊዜ አመጣህ በማለት፡፡
   - ጌታችን በምሴተ ሐሙስ የጸለየበት ስለሆነ፡፡ *ማቴ 26፡20-26፡፡* "በመኝታዬም አስብሃለሁ፥ በማለዳም እናገርልሃለሁ" *መዝ 62፡6፡፡*
7. *መንፈቀ ሌሊት*
   - ጌታ የተወለደበት፣ የተጠመቀበት፣ የተነሳበት ዳግም የሚመጣበት ስለሆነ ይህን ለማሰብ እጅን ታጥቦ ወይም በምራቅ ወይም በትንፋሽ እንፋሎት ታጥቦ መጸለይ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን የታዘዘ ነው፡፡ *ሉቃ 2፡1-4፣ ማቴ 28፡1፣ ማቴ 16፡1፣ ሉቃ 24፡1፣ ዮሐ 20፡21፣ መዝ 132፡1-3፣ መዝ 1፡1-3፡፡* "በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር" *የሐዋ. ሥራ 16፡25፡፡*

*ሥርዓት*

1. ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ልዩ ችግር ካላጋጠመው በቀር በሰባቱም ጊዜያት መጸለይ ይገባዋል፡፡ ልዩ ችግር ከገጠመው ግን የጠዋትና የማታውን ጸሎት የመጸለይየ ግዴታ አለበት፡፡
2. ባልና ሚስት በምንም ጊዜ እጃቸውን ከመታጠብ በስተቀር በገላ መታጠቢያ መታጠብ ሳያስፈልጋቸው በአዳራሹና በእልፍኙ ወይም በጓዳና በበሩ ሆነው በአንድ ወቅት እንዲጸልዩ ታዟል፡፡ ሩካቤያው ንጹሕ ስለሆነ፡፡
3. ከባልና ከሚስት አንዳቸው ያላመኑ ቢሆኑ ያመነው (ክርስቲያን) ተለይቶ እንዲጸልይ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዛል፡፡
4. ከቤተ ክርስቲያናችን መላዕክት አይታጡምና አጋንንት እንዳይሰለጥኑብን ቢቻል የነግሁና የሠርኩ ጸሎት ዘወትር በቤተ ክርስቲያን እንዲሆን ታዟል፡፡ ይልቁኑ ተግባረ ነፍስ በሚሠራባት በእሁድ ሰንበት በቤተ ክርስቲያን በመገኘት በአንድነት መጸለይ ይገባል፡፡
5. ደዌ ሕመም ሳያገኛቸው በዕለተ እሁድ ከቤተ ክርስቲያን የቀረ ከምዕመናን ጉባኤ እንዲለይ ተወስኗል፡፡ የታመመም ከሆነ ቅዱስ ዘይት ተቀብቶ፣ ጠበል ጠጥቶ፣ ወንጌልና መስቀል ተሳልሞ፣ ቃለ እግዚዘአብሔር ሰምቶ ፈውሰ ሥጋን ማግኘት የማይችል ከሆነው በቀር ከቤተ ክርስቲያን እንዳይቀር፤ የሚያውቁትም እንዲጸልዩለት ሕገ-ቤተ ክርስቲያን ያዛል፡፡

# ለጸሎት ምን ተጨማሪ ሥርዓት አለ?

1. ካህናት ብቻ የሚጸልዩት ጸሎትም ተለይቶ ተወስኗል፡፡ ይኸውም፡-
   ሀ. ጸሎተ ጥምቀተ ክርስትና
   ለ. ጸሎተ ቅዳሴ
   ሐ. ጸሎተ ሲመት (ክህነት)
   መ. ጸሎተ ባርኮተ ታቦት
   ሠ. ጸሎተ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያን
   ረ. ጸሎተ ተክሊል
   ሰ. ፍትሐት ዘወልድ (ጸሎተ ፈውስ - ቀንዲል)
   ሸ. ጸሎተ ፍትሐት (ጸሎተ ሙታን)
   ቀ. ጸሎተ ዘይት (ሜሮን ሲያከብሩ)፣ አሥራቱን፣ በኩራቱን፣ ስዕለቱን ሲቀበሉ የሚጸልዩት ነው፡፡

- በጸሎቱም መጨረሻ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም እአንዲሉ ታዟል፡፡ *2ኛ ቆሮ 13፡14፡፡*

2. መነኮሳት ጊዜያተ - ጸሎት አልተወሰነላቸውም፡፡ ምክንያቱም የመነኮሳት ጸሎት በሌሊትም በቀንም ስለሆነ ተግባራቸውም ይኸው ጸሎት ብቻ ነውና፡፡
3. ከመመገብ አስቀድሞ ለበረከት፡ ለቀድሶ ሥራይ መርዝ ቢኖርበት እንዲጠፋ፣ ከተመገቡ በኋላ ከኃጢአት ለመጠበቅ፡ ለጤንነት፡ በሚሠሩት ትሩፋት ለመጽናት ይችሉ ዘንድ ጸሎተ ማዕድ ለክርስቲያን ሁሉ ታዟል፡፡ *ማቴ 14፡19፡፡*
4. መነኮሳት ከባዕታቸው ሲወጡና ሲገቡ የሚጸልዩት እነርሱው በአጭር የሠሯት ጸሎት አለች፡፡ ይህም አማትቦ አቡነ ዘበሰማያት መድገም ነው፡፡
5. ከዚህ ሌላ መከራን ለማራቅ የሚጸለይ የፈቃድ ጸሎት አለ፡፡ ይኸውም በሁለት ይከፈላል፡፡
   ሀ. ስለ ራስ መከራ፡፡
   ለ. ስለ ሌላው መከራ የሚጸለይ ጸሎት ነው፡፡ ይህም ካህናት ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የሚጸልዩት ነው፡፡
6. መጽሐፍ ያልከለከላት፣ ፈቃድ የሚፈጸምባበት ጸሎት አለች፡፡ ይህችውም፡-
   ሀ. ልጅ ስጠኝ
   ለ. ጥበብ አድለኝና የመሳሰለውን ሁሉ ሽቶ በስዕለት መልክ የምትቀርብ ጸሎት ናት፡፡
7. መንፈሳውያን አባቶች ለመንፈሳውያን ልጆቻቸው የሚጸልዩት ጸሎት አለ፡፡
8. ተወግዞ ከተለየ ካህን ጋር ወይም ከማያምን ጋር በቤተ ክርስቲያን ወይም በቤት የጸለየ ካህን ቢሆን ከሥልጣኑ ከአባልነቱ፣ አማኝ ቢሆን ከምዕመንነቱ እንዲሻር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ያዛል፡፡ "ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ…" *2ኛ ቆሮ 6፡14-16፡፡*
9. ካህን በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ሳለ ታላቅ እንግዳ እንኳ ቢመጣ ዲያቆናት ይቀበሉት እንጂ ካህኑ ጸሎቱን እንዳያቋርጥ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተወስኗል፡፡ *ማቴ 12፡46-50፡፡*

ይቆየን፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡